


# ተገርዘሻል?

በመላው ኖርዌይ በሚገኙ የጤና ተቋሞች የሴት ብልትን
የመክፈት ኦፕራሲዮን አገልግሎት ይሰጣል

**www.nkvts.no / www.nakmi.no**
Informasjonsbrosjyre om åpnende operasjoner for kjønnslemlestede, på amharisk.

ይህ ጥራዝ የተዘጋጀው፤ በ Nasjonalt kunnskapssenter om vold og traumatisk stress (NKVTS) ሲሆን፣ ጥራዙ በኤሌክትሮኒክስ መረጃ በድረ ገጻችን www.nkvts.no

ይገኛል። የህትመት ጥራዙን ደግሞ postmottak nkvts.unirand.no ወይም በስልክ ቁጥር 22 59 55 00

በመደወል ማዘዝ ይቻላል። ግርዛትን ለመከላከል መንግስት ባወጣው መመሪያ ሰነድ (Regjeringens handlingsplan) 2008-2011 መሰረት NKVTS የሚባለው ተቋም ኣገር ኣቀፍ የጥናት አና ምርምር ተግባር ላማካሄድ የሚችል ኣካል አንዲያቋቁም ሃላፊነት ተሰጥቶታል። NKVTS ይህን በሚመስል ጉዳይ ላይ የምርምርና የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፥ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ትምህርትና ሰልጠና ይሰጣል።

አርትዖትና መገናኛ Christine Istad
ፎቶ፥ www.luth.no og Lars Sørli

# በኦፕራሲዮን መክፈት

## ተገርዘሻል? ለማንኛውም የግርዛት ኣይነት ከተጋለጥሽና፣ ወይም ድርጊቱ ከተፈጸመብሽ ርዳታ መጠየቅ ትችያለሽ

በመላዋ ኖርዌይ ክልል ባሉ የጤና ተቋሞች የሴት ብልትን የመክፈት ኦፕራሲዮን አገልግሎት ይሰጣል።
በግርዛቱ ምክንያት ነው ህመሙ የተሰማኝ ብለሽ ካሰብሽ በተቻለሽ መጠን በአፋጣኝ ርዳታ እንድታገኚ ማድረግ አለብሽ።
የብልት መክፈቻ ኦፕራሲዮን ተግባሩ የብልት ከናፍሮችን የተሰፋበትን ስፌት ማላቀቅ ነው።

## የተሰፋ ብልትን የመክፈት ጠቀሜታ

በኦፕራሲዮን የተሰፋ ብልትን የመክፈት ጠቀሜታው፣

- በግርዛቱ ምክንያት የመጣውን ህመምና፥ አለመመቸት ለማስወገድ፣
- ከኦፕራሲዮኑ በኋላ በቀላሉና በፍጥነት መሽናት ሲቻል፣ ማህጸንን ደግሞ ኢንፌክሽን በቀላሉ ሊያጠቃው አይችልም።
- የመንፈር ወይም ውሃ መቋጠርን ለመከላከል፣
- ማርገዝ ሲፈልጉ ችግር እንዳይገጥማቸው ይረዳል፣
- የወር አበባን ፍሰት በቀላሉና በትክክለኛው መንገድ እንዲፈስ ማድረግ፣
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ለብዙዎች ጥሩ ስሜት እንዲኖራቸው ይረዳል።

## ክብረ ንጽህና

ስፌቱን በኦፕራሲዮን መክፈት በምንም ዓይነት ሁኔታ ክብረንጽህናን አይነካም። ኦፕራሲዮኑ በምንም አይነት ከክብረንጽህና ጋር ግኑኝነት የለውም። ስፌቱ ከተከፈተም በኋላ ክብረንጽህና እንደተጠበቀ ሆኖ መኖር ይቻላል።



# በሴቶች ክሊኒክ ውስጥ ምን ይከናወናል?

እድሜዋ 16 ዓመት የሞላት ልጅ በኦፕራሲዮን ስፌቱ እንዲከፈትላት በራሷ የመወሰን መብት አላት። አንቺ ራስሽ ከሴቶች ክሊኒክ ጋር ግኑኝነት ማድረግ ትችያለሽ። የህክምና መርጃ ጣቢያው ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ቋሚ ሃኪምሽ ወደ ሴቶች ክሊኒክ ሊመራሽ ይችላል። ሰው አስከትለሽ  አብረሽ ልትሄጂ ትችያለሽ። ወሳኙ ግን ራስሽ ነሽ።

## ምክክር

ሀኪሙ ርዳታ ወደ ሚሰጥበት ቦታ ከመራሽ በኋላ፣ ወይም ከሴቶች ክሊኒክ ጋር ግንኙነት ካደረግሽ በኋላ፣ ፍላጎቱ ካለሽ  ለምክክር ትጠሪያለሽ። ምክክሩ ለምን ስፌቱን መክፈት እንደሚያስፈልግ፥ ሂደቱም እንዴት እንደሚከናወን፥ ወይም ልታነሺያቸው ስለምትፈልጊያቸው የተለያዩ ችግሮች ሊሆን ይችላል። በዚያው አጋጣሚ በተገኘሽበት ቀን የህክምና ርዳታ ልታገኚ ትችያለሽ። ቀጣዩ ደግሞ የኦፕራሲዮኑን ጊዜ መጠበቅ ነው። ከመጀመርያው የምክክር ጊዜ ጀምሮ በኦፕራሲዮን ለመክፈት የምታገኚው ርዳታ የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ብዙ ጊዜ ግን ከሁለት ወራት አይበልጥም።

## ኦፕራሲዮኑ

የብልት መክፈት ኦፕራሲዮን ዋና አላማው የሴቶችን ብልት ከመገረዛቸው በፊት ወደነበረበት ትክክለኛና ተፈጥሮአዊ የኣካል ቅርጽ እና ይዘት እንዲመለስ ለማስተካከል እንዲሁም ህመምንና አለመመቸትን ለመቀነስ ነው። የብልት መክፈቱ ጥረት የሚቻል ከሆነ እና ፍላጎቱ ካለሽ፣ በቂንጥር ዙሪያ ያለውን አካባቢ ሊያካትት ይችላል። ድንገት የግርዛቱ አይነት ውስብስብ እና የከፋ ከሆነ ብልትን ወደ ወደቀድሞ ተፈጥሮአዊና ትክክለኛ የአካል ቅርጽ እና ይዘት ለመመለስ ኣስቸጋሪ ይሆናል። ስለሆነም ስለቀጣዩ ኦፕራሲዮን ሃኪምሽ ከአንቺ ጋር በመመካከር ፕሮግራም ያወጣል። ቀዶ ጥገናው የሚካሄደው በፖሊክሊኒክ ውስጥ ነው። ይህም ማለት ሆስፒታል የሚያስተኛ አይደለም ማለት ነው። ቀዶ ጥገናው ሲካሄድ በማደንዘዣ ሲሆን የሚወስደውም 30 ደቂቃ ነው። ለአቅመ አዳም ላልደረሱ ሴት ልጆች የሚሰጣቸው ማደንዘዣ መላ አካልን የሚያደነዝዝ ናርኮስ ነው። ውሃ የቋጠረ ወይም የነፈረ ሁኔታ ካለና አስቸጋሪ ከሆነ የቀዶ ጥገናው ጊዜ ወደ አንድ ሰዓት ሊወስድ ይችላል። ከኦፕራሲዮኑ በኋላ በዚያው ቀን ወደ ቤትሽ መሄድና ማረፍ ትቺያለሽ። ስለኦፕራሲዮኑ ሁኔታና የቁስል እንክብካቤ የሚያስረዳ ገለጻ ከተደረገልሽ በኋላ ደግሞ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት ማዘዣ ይሰጥሻል።

ከተፈጥሮ አንጻር ሰውነት የተስተካከለ ነው።


ስፌቱን በኦፕራሲዮን መክፈት ብዙ ጠቀሜታ አለው። ለመሽናት ቀላል ነው። በማህጸን ውስጥ የሚሰማው ህመም ሊጠፋ ይችላል። የወር አበባ በቀላሉ ሊፈስ ይችላል። ለኢንፌክሽን የመጋለጡ ሁኔታ የቀነሰ ነው።

# ከቀዶ ጥገናው በኋላ

## የህመም ማስታገሻ መድሃኒት

ሃኪሙ ለህመሙ ማስታገሻ የሚሆን የመድሃኒት መግዣ ማዘዣ ለመጀመርያዎቹ ቀናት ሊጽፍ ይችላል።

## የህመም ፈቃድ

ለብዙዎቹ ሰዎች የህመም ፈቃድ አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን አልፎ አልፎ የህክምናው እርዳታ ቀጣይነት ካለው ሃኪሙ የተወሰኑ ቀናት የሃኪም ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ ከስነ-ልቦና ሃኪም ጋር ለመነጋገር እድሉን ማግኘት ትቺያለሽ። ስለ ቀዶ ህክምናው ወይንም የህክምና ርዳታ ስለማግኘትሽ ማስረጃ ካስፈለገሽ ከክሊኒኩ ማግኘት ትችያለሽ ።

## የኦፕራሲዮኑ ክር

የኦፕራሲዮኑን ክር ማውጣት አስፈላጊ አይደለም። ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንታት በኋላ በራሱ ሊረግፍ ይችላል።

ብዙውን ጊዜ ከኦፕራሲዮኑ በኋላ ወደ ክሊኒኩ ዳግመኛ መጥቶ የምርመራ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ አይደለም።

## የግብረ ስጋ ግንኙነት

ከኦፕራሲዮኑ በኋላ ወዲያውኑ ቁስሉ ለኢንፌክሽን ስለሚያጋልጥ አደገኛ ነው። ስለዚህም አንድ አዋቂ/ወጣት ሴት ከአራት እስከ ስድስት ሳምንታት ከኦፕራሲዮኑ በኋላ ግብረ ስጋ ግኑኝነት ማድረግ የለባትም።

## በርግዝና ወቅት ስለማስከፈት

በእርግዝና ወቅት የተሰፋ ማህጸን የጽንሱን እድገት ለመከታተል አስቸጋሪ ስለሚሆን በመውለጃ ጊዜም የጤና መወሳሰብ ችግር ይፈጥራል። ለምሳሌ ግርዛት የውሃ ሽንትን ያለ ወቅቱ በጊዜ ከመፍሰሱ ጋር ተያየዞ ችግር ሊያስከትል ይችላል። አንድ ብልቷ የተሰፋ ያረገዘች ሴት፣ የመውለጃዋ ቀን ከመድረሱ በፊት ስፌቱ መፈታት እንዳለበት እንመክራታለን። አንድ የጸነሰች ሴት የመውለጃዋ ቀን ከመድረሱ በፊት ስፌቱ በቅድሚያ መከፈት እንዳለበት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የምንመክረው ኦፕራሲዮኑ መከፈት ያለበት ከ16ኛው የርግዝና ሳምንት ጀምሮ ነው። ኦፕራሲዮኑ የሚካሄደው ከውጭ በኩል ባለው የብልት አካል ላይ ስለሆነ፣ በጽንሱ ላይ ምንም አይነት አደጋ አይፈጥርም።



አደገኛ አይደለም

ክብረ ንጽህና እንደተጠበቀ ይቀጥላል

ማደንዘዣና ህመም ማስታገሻ ይሰጣል

ለተወሰነ ቀን መረጋጋት ያስፈልጋል

በብዙ መቶ ለተቆጠሩ ሴቶች ስፌቱን የመክፈት

አገልግሎት ሰጥተናል

የተካበተ የሥራ ልምድ አለን

ከራስዎት የሚከፍሉት የግል ወጪ በትንሹ

በግምት 300 ክሮነር ቢደርስ ነው

ሳራ ካህሳይ አዋላጅ – በኦስሎ ዩንቨርስቲ ሆስፒታል ኡሌቮል

# መረጃ ቢያስፈልግሽ

በሁሉም የጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ክልሎች ልዩ ኃላፊነት ያላቸው፣ የሴቶችን ግርዛት የሚከታተሉ የሴቶች ክሊኒኮች ይገኛሉ። ክሊኒኮቹ የሚሰጡት አገልግሎት፣ ምክክር፣ ምርመራና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በኦፐራሲዮን የመክፈት አገልግሎትን በቀኑ ይሰጣሉ። ከክሊኒኩ ጋር በቀጥታ በመገናኘትም ሆነ ወይም ሀኪምሽ፥ ከጤና ነርሷ ወይም ከአዋላጇ ወደ ክሊኒኩ ልተመሪ ትችያለሽ። እነሱም የአንቺን ሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። ከነሱም ለጥያቄዎችሽ መልስ ማግኘት ትችያለሽ። ተማሪ ከሆንሽም፣ የትምህርት ቤቱን የጤና አገልግሎት ክፍል ማማከር ይቻላል።

**Universitetssykehuset i Nord-Norge** (ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል በሰሜን ኖርወይ) , Tromsø በሴቶች ክሊኒክ ውስጥ የማህጸን ክሊንክ ወይም የማዋለጃ ክልኒንክን በስልክ ቁጥር 77 62 60 00 በመደወል ያነጋግሩ።

**Haukeland Universitetssykehuset** (ሃውከላንድ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል) , Bergen የሴቶች ክሊኒክን በቀጥታ ማዞርያ ስልክ ቁጥር 05300 ማግኘት ይቻላል።

**St. Olavs Hospital** (ሰይንት ኡላቭ ሆስፒታል) , Trondheim በቀጥታ የሴቶች ክሊንክ ብሎ በስልክ ቁጥር 72 57 12 12 በመደወል ያነጋግሩ።

**Stavanger Universitetssykehus (SUS)** (ስታቫንገር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል) በቀጥታ የሴቶች ክሊንክን በማዞርያ ቁጥር 05151 በመደወል ያነጋግሩ።

**Oslo Universitetssykehus Ullevål** (ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ኡለቮል) ዘወትር አርብ እስከ ቀኑ 12 ሰዓት ድረስ በስልክ ቁጥር 22 11 98 44 በመደወል ተጠሪዋን ሳራ ካህሳይን በቀጥታ ስልክ ቁጥር 938 98 903 በመደወል ያነጋግሩ።

**Oslo Universitetssykehus Rikshospitalet** (ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ሪክስሆስፒታል) የሴቶች ክሊኒክን በስልክ ቁጥር 23 07 00 00 በመደወል ያነጋግሩ።

NAKMI
Nasjonal kompetanseenhet for minoritetshelse
Nasjonalt kunnskapssenter
om vold og traumatisk stress a/s